# መመሪያ ቁጥር 1079/2017

# የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስርዓት መመሪያ

ግንቦት፣ 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 1079/2017

## የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስርዓት መመሪያ

የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው በሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚለጠፈውን የኤክሳይዝ ቴምብር ዓይነት እና በእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ቴምብር የሚለጠፍበት እቃ ምድብ እና ንዑስ ምድብ ላይ ቴምብሩ የሚለጠፍበትን አኳኋን መወስን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኤክሳይዝ ቴምብር ስርዓት እና አጠቃላይ የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታን በመወጣት ረገድ በሚኖረው አፈጻጸም ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀፅ 35 ለገቢዎች ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 29(1) እና በአንቀፅ 42(2) ከገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ውክልና መሰረት የገቢዎች ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 1079/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ "ፊዚካል የኤክሳይዝ ቴምብር" ማለት በጅምላ ወይም በችርቻሮ በሚሸጡ አግባብነት ባለው የእቃዎች መያዣ ላይ በዚህ መመሪያ በተወሰነው መስረት የሚለጠፍ ተለጣፊ ቴምብር ነው።

2/ "ዲጂታል የኤክሳይዝ ቴምብር" ማለት በፊዚካል የኤክሳይዝ ቴምብር ፈንታ በእቃዎች መያዣ ላይ በቀጥታ የሚታተም ኮድ ነው።

3/ "ባለአራት ማዕዘን ቴምብር" ማለት የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ግዙፍ የኤክሳይዝ ቴምብር ሲሆን አግባብነት ባላቸው እቃዎች መያዣ ክዳን፣ መዝጊያ ወይም ማሸጊያ ላይ ከላይ ወደታች እንዲለጠፍ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

4/ "ክብ ቴምብር" ማለት ክብ ቅርጽ ያለው የኤክሳይዝ ቴምብር ሲሆን ከጠርሙሶች፣ከቆርቆሮ ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ባላቸው ግብዓቶች በተሰሩ መያዣዎች ክዳን ላይ በክብ መልክ እንዲለጠፍ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

5/ "ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ መልክ የተመረተ መጠጦች" ማለት በውስጣቸው እንደ ስኳር፤ የፍራፍሬ ጭማቂ፤ የአትክልት ጭማቂ፤ የተፈጥሮ ወይም አርተፊሻል ጣዕም ሰጪ ነገር፣ ውሃ፤ የሚኒራል ውሃ፤ ቅጠላ ቅጠል፤ ቅመማ ቅመም እና ሌሎች ከአትክልት የሚገኙ ነገሮች እና/ወይም ካርቦንዳይ ኦክሳይድ የተጨመረባቸው የአልኮል መጠጦች ናቸው።

6/ አልኮል የሌለባቸው ስኳር በማጣፈጫነት የተጨመረባቸው መጠጦች" ማለት አልኮል የሌለባቸው መጠጦች፤ ካርቦን የተጨመረባቸው መጠጦች እና ጣፋጭነት ያላቸው መጠጦች ናቸው።

7/ "መያዣ" ማለት ከጠርሙስ፤ ከፕላስቲክ፤ ከወረቀት ወይም ከቆርቆሮ የተሰሩ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚታሸጉበት እቃን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው መያዣዎችን የሚጨምር ነው።

8/ "አግባብነት ያላቸው እቃዎች" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩ እቃዎች ናቸው።

9/ በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት እና ሀረጎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የተሰጣቸውን ትርጉም በመያዝ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር እና በጉምሩክ ኮሚሽን ክትትል እና ቁጥጥር በሚደረግባቸው አገር ውስጥ በሚመረቱ እና ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገቡ እቃዎች</u>

በሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል፦

1/ የአልኮል መጠጦች፤

2/ አልኮል እና አልኮል አልባ ቢራ፤

3/ የወይን ጠጅ ወይም የተጣራ አልኮል የታከለበት ወይን ጠጅ እና ተመሳሳይ የአልኮል መጠናቸው ከ0.5% በላይ የሆነ ምርቶች፤

4/ ለሰው መጠጥነት የሚውሉ እና ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ መልክ የተመረቱ መጠጦች፤

5/ ሲጋራ፣ ትምባሆ፣ በራስ የተጠቀለለ ትንባሆ፣ የሲጋራ ወረቀቶች፣ ቢዲስ፣ ክሬቴክስ፣ ጭስ የሌለው ትምባሆ፣ ሲጋራ፣ ሺሻ፣ የቧንቧ ትምባሆ እና ሌሎች የሚቃጠሉ ወይም የማይቃጠሉ የትምባሆ ምርቶች በሙሉ ለሰው ልጅ ፍጆታ የሚውሉ ሲጋራ እና ሌሎች የትምባሆ ውጤቶች፤

6/ የታሸገ ውሃ፤

7/ ሽቶዎች

8/ ከአልኮል መጠጥ ጋር የሚደባለቁትን ጨምሮ አልኮል የሌለባቸው መጠጦች፤ ካርቦን የተጨመረባቸው መጠጦች እና ጣፋጫነት የተጨመረባቸው መጠጦች፤

5. <u>በጅምላ እና በችርቻሮ በሚሸጡ እቃዎች መያዣ ላይ የሚለጠፍ የኤክሳይዝ ቴምብር</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩ ለጅምላ እና ለችርቻሮ ገበያ በሚቀርቡበት አኳኋን የታሸጉ እቃዎች በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኤክሳይዝ ቴምብር አይነቶች እና የሚለጠፉበት ሁኔታ</u>

6. <u>ፊዚካል የኤክሳይዝ ቴምብር</u>

1/ ፊዚካል የኤክሳይዝ ቴምብር በሚከተለው አኳኋን ይለጠፋል፦

ሀ) ባለአራት ማዕዘን ቴምብር የሚለጠፈው በእያንዳንዱ የእቃ መያዣ ክዳን ላይ ከላይ ወደታች ይሆናል፤

ለ) ክብ ቴምበር የሚለጠፈው ጠርሙሶችን በሚመለከት በክዳኑ የላይኛው ክፍል ላይ ሲሆን የቆርቆሮ ጣሳን በሚመለከት በጣሳው መክፈቻ ላይ ነው።

2/ በዕቃዎች ላይ የተለጠፈው ፊዚካል ቴምብር ፦

ሀ) ባለ አራት ማዕዘን ቴምብር በሚሆንበት ጊዜ የእቃው መያዣ ሲከፈት ሊጠገን በማይችልበት ደረጃ የሚቀደድ ወይም የሚበላሽ መሆን አለበት።

ለ) ክብ ቴምብር ከእቃው ላይ ሲነሳ ሊጠገን በማይችልበት ደረጃ እንዲበላሽ ሆኖ በጥንቃቄ መለጠፍ አለበት።

ሐ) ፊዚካል ቴምብር የወረቀት ክብደት ከ50-70 ግራም የሚመዝን መሆን አለበት

መ) ፊዚካል ቴምብር መልሶ ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል መሆን አለበት።

ሠ) ፊዚካል ቴምብር ከማሸጊያው ላይ ሳይበላሽ ማንሳት እንዳይቻል ለማድረግ በቂ ማጣበቂያ ያለው መሆን አለበት።

3/ በፊዚካል ቴምብር ምስጢራዊ ምልክቶች፣

ሀ) ፊዚካል ቴምብር የሚታይ፣ በከፊል የሚታይ፣ የማይታይ (በአጋዥ መሳሪያ የሚታይ) እንዲሁም ፎረንሲክ ምልክቶች ይኖሩታል፣

ለ) ምስጢራዊ ምልክቶች ኮፒ ወይም አመሳስሎ መስራት የሚቻል አይሆንም፣

ሐ) ምስጥራዊ ምልክቶች ኬሚካል በመጠቀም የሚጠፉ አይደለም፣

7. ዲጂታል የኤክሳይዝ ቴምብር

1/ ዲጂታል የኤክሳይዝ ቴምብር እቃው በመያዣው ውስጥ በሚታሸግበት ጊዜ የሚታተም ሲሆን በቴምብር ማንበቢያ አማካኝነት የተጻፈው ጽሁፍ የሚነበብ መሆን አለበት።

2/ ተመላሽ የሚሆኑ ጠርሙሶች በመያዣው ክዳን ላይ መታተም አለበት።

3/ መልሰው ጥቅም ላይ በማይውሉ መያዣዎች ላይ የዲጂታል ቴምብር የሚታተመው በመያዣው ላይ በሚታይ ቦታ ወይም በክዳኑ ላይ ይሆናል።

8. የሚለጠፈው ቴምብር አይነት

በአንቀጽ 4 በተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚለጠፈው የኤክሳይዝ ቴምብር አይነት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ የተመለከተው ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## የኤክሳይዝ ቴምብር ለማግኘት ማመልከቻ አቀራረብ እና የሚለጠፍበት ጊዜ

9. ለኤክሳይዝ ቴምብር ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1/ ለኤክሳይዝ ታክስ የተመዘገቡ ሰዎች ለእያንዳንዱ ለሚያመርቱት ምርትና ለመያዣያው እንዲሁም አስመጪዎች ለዕቃውና ለመያዣው ተገቢነት ያለውን የኤክሳይዝ ቴምብር ለማግኘት በመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በመጠቀም ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው።

2/ ለኤክሳይዝ ታክስ የተመዘገቡ ሰዎች ማመልከቻ የሚያቀርቡት ለተመዘገቡበት የኤክሳይዝ ታክስ ለሚከፈልበት እቃ ብቻ ይሆናል።

3/ እያንዳንዱ አምራች ወይም አስመጪ የሚያቀርበው ማመልከቻ በምርቱ አይነት፤ በማሸጊያው ምንነት እና የተመዘገበው ሰው በሚጠቀምበት የማሸጊያ መሳሪያ ፍጥነት ሊለያይ ይችላል።

4/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ለምርቱ የተወሰነው የፊዚካል ቴምብር ቢሆንም አምራቹ ፈጣን የማሽጊያ መሳሪያ የሚጠቀም ከሆነ ዲጂታል ቴምብር እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ይችላል።

5/ የገቢዎች ሚኒስቴር የተመዘገበው ሰው የሚጠቀምበት የማሽጊያ መሳሪያ ፈጣን መሆኑን ካረጋገጠ በተጠየቀው መሰረት ሊፈቅድ ይችላል።

10. <u>**የኤክሳይዝ ቴምበር የሚለጠፍበት ጊዜ**</u>

1/ የኤክሳይዝ ቴምብር በሚለጠፍባቸው እቃዎች ላይ ሁሉ ምርቱ የኤክሳይዝ ቴምብር መስመርን ከማለፉ በፊት የኤክሳይዝ ቴምብር ወይም ምልክት ሊለጠፍባቸው ይገባል።

2/ የኤክሳይዝ ቴምብር ወይም ምልክት ሳይለጠፍባቸው ከተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ እቃዎቹን ከኤክሳይዝ ታክስ መስመር ውጪ ይዞ የተገኘ ሰው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል።

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም "የኤክሳይዝ ታክስ መስመር" ማለት፦

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የተመዘገበው ሰው የማምረቻ ቦታ የሚመረቱ እቃዎች በሚመለከት ምርቱ በመያዣው ውስጥ ሲታሸግ፤

ለ) ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር የሚለጠፍበት ሁኔታን በሚመለከት፦

(1) የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጠፍባቸው እቃዎች ወደ አገር ውስጥ ወደ ሚገቡበት የጉምሩክ መዳረሻ የደረሱ ከሆነ፤ ለኤክሳይዝ ቴምብር እና ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ወጪ ሙሉ በሙሉ በአስመጪው የሚሸፈን ሆኖ፤ የጉምሩክ ኮሚሽን ቴምብሩን በመሳሪያ አማካኝነት ይለጥፋል፤ ወይም

(2) የጉምሩክ ኮሚሽን እቃዎች ወደ አገር ከመግባታቸው ቢያንስ ከ5 ቀናት በፊት የቅድሚያ ማስታወቂያ የደረሰው ከሆነ እቃዎቹ የኤክሳይዝ ቴምብር መለጠፊያ መሳሪያ ወዳለው ወደ ተፈቀደለት የጉምሩክ መጋዘን እንዲጓጓዙ ማድረግ ይቻላል፤ ወይም

(3) አስመጭው የሚያቀርበው ማመልከቻ በጉምሩክ ሲታመንበት እቃዎቹ በሚመረቱበት አገር በሚገኝ የማምረቻ ቦታ የኤክሳይዝ ቴምብር ይለጠፍባቸዋል።

11. <u>**ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች የሚሰጥ የቅድሚያ ማስታወቂያ**</u>

1/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎችን በሚመለከት እቃዎቹ ከመድረሳቸው ከ5 ቀን በፊት አስመጪው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ በተፈቀደ ቅጽ የተዘጋጀ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለጉምሩክ ኮሚሽን መድረስ አለበት፦

(ሀ) የቅድሚያ ማስታወቂያው የቀረበበት ቀን፤

(ለ) እቃዎቹ የተመረቱበት አገር፤

(ሐ) እቃዎቹ በተመረቱበት አገር ያለውን አምራች ስም፤

(መ) በኢትዮጵያ ያለውን አስመጪ ስም፤

(ሠ) እቃውን ወደ አገር የሚገባበትን ቦታ፤

(ረ) እቃው አገር ውስጥ የሚደርስበትን ቀን እና ሰዓት በግምት፤

(ሰ) የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ቁጥር፤

(ሸ) የምርቱ አይነት፤

(ቀ) የእያንዳንዱ መያዣ አይነት እና መጠን፤

(በ) የእያንዳንዱ መያዣ ብዛት እና መጠን፤

(ተ) በእያንዳንዱ የምርት አይነትና የማሸጊያውን መጠን ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ዋጋ፤

(ቸ) እቃዎቹ የሚላኩበትን በእቃዎቹ ላይ የቴምብር ቀረጥ የሚለጠፍበትን ቦታ፤

2/ እቃዎቹ ለቅድሚያ ማስታወቂያ ከተቀመጠው ጊዜ በፊት የደረሱ ከሆነ እንደ ደረሱ መስተናገድ ይችላሉ።

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ቢኖርም አስመጪው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ዘግይቶ ቢያሟዉቅም እንደ ምክንያቱ ሁኔታ ኮሚሽኑ ሊያስተናግደው ይችላል።

4/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 እና 3 የተደነገገው የእቃዎች አይነት የጉምሩክ አስገዳጅ ሰነዶችን የሚሟላው፣ የጉምሩክ ቀረጥ እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በጉምሩክ መዳረሻዎች ይሆናል።

5/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜያዊነት የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው የኤክሳይዝ ቴምብር ወደ ሚለጠፍባቸው ቦታዎች የሚጓጓዙት በአገር ውስጥ የእቃዎች ዝውውር የትራንዚት ሰነድ አማካኝነት ነው።

6/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም የትምባሆ ውጤቶች በማምረቻ ቦታቸው ወይም ወደ አገር በሚገቡበት የጉምሩክ መዳረሻ አግባብነት ያለው የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል።

## ክፍል አራት

## ለምዝገባ ስለሚቀርብ ማመልከቻ እና ቁጥጥር

12. የማምረቻ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማስረጃ

1/ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ማምረቻ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ አለበት።

(ሀ) አግባብነት ባለው የመንግስት አካል የተሰጠ የንግድ ፈቃድ፤

(ለ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የአክሲዮኑ ዋና ስራአስኪያጅ ፋይዳ መታወቂያ፤

(ሐ) አመልካቹ የሚጠቀምባቸውን የአመራረት ሂደቶች፣ እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሳሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ ኮንቴነሮች፣ መሳሪያዎች፤መገጣጠሚያዎች።

(መ) የአሰራር ሂደቱን የሚገልፅ የፅሑፍ ማብራሪያ፣

(ሠ) ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የማምረቻ ህንፃ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እና ህንፃው፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች የሚገኙበትን ሁኔታ እና አከባቢውን ፤

(ረ) የእያንዳንዱ በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሳሪያ የማምረቻ አቅም በዝርዝር፤

(ሰ) የማምረቻ መሳሪያዎችን ማስረጃዎችን እና መግለጫዎች ፤

(ሸ) ዝርዝር የንግድ ስራ እቅድ፤ የሚያመርታቸውን ምርቶች አይነት፤ የመያዣውን/የማሸጊያውን አይነት፤ የምርቱን መለያ ስም፤ በእያንዳንዱ የምርት መለያ ስም፤ ከአንድ እስከ ሶስት አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለማምረት ያቀደውን የምርት ብዛት፤

(ቀ) የንግድ ስራውን ወጪ የሚሸፍንበትን መንገድ፤ የፋይናንሱ ምንጭ ብድር ከሆነ የአከፋፈሉን ሁኔታ እና የመክፈያውን ጊዜ ጨምሮ ስለብድሩ ዝርዝር መረጃ፤

(በ) የፋብሪካው ቅጥር ግቢ በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራዩን ውል፤ የፋብሪካው ቅጥር ግቢ በድርጅቱ ባለቤትነት ስር ያለ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፤

(ተ) የገበያውን ስትራቴጂ እና ለማካሄድ የታቀደውን ገበያ ዓይነት፤

(ቸ) የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታውን ለመወጣት የሚከተለውን የኤክሳይዝ ታክስ አሰራር እና ቁጥጥር፤

(ኀ) ሊከናወን የታቀደውን የሽያጭ ዓይነት የሚያስረዳ መግለጫ እንደ ችርቻሮ፣ጅምላ፣ ኤክስፖርትን ጨምሮ ሌሎች ተመሳሳይ የሽያጭ ዓይነት መግለጫዎችን ይጨምራል፤

(ነ) የጥሬ እቃ አቅርቦት አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ የተፈረሙ ውሎችን ጨምሮ የጥሬ እቃ አቅራቢዎቹን የሚመለከት ማስረጃ፤

2/ የገቢዎች ሚኒስቴር እንደ ጉዳዩ ዓይነት ተጨማሪ መረጃ ሊጠይቅ ይችላል።

3/ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ አስቀድሞ የተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከዚህ በፊት ያላቀረባቸውን ወይም ከምዝገባው በኋላ የተደረገ ለውጥ ካለ ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።

## 13. <u>የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች</u>

1/ የተፈቀደለት አምራች ከሩቅ ሆኖ የምርት ሂደት፣የጥሬ እቃ አቅርቦትና መላውን የፋብሪካውን እንቅስቃሴ መከታተል የሚያስችል የቴክኖሎጂ መሳሪያ በፋብሪካው ውስጥ መገጠም አለበት።

2/ የሚገጠመው የቴክኖሎጂ መሳሪያ፦

(ሀ) የገቢዎች ሚኒስቴር በማናቸውም ጊዜ በመከታተያ መሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችል፤

(ለ) ምስሎችን እና ሌሎች መረጃዎችን አስተማማኝ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማከማቸት የሚችል እና ዲጂታል በሆነ ዘዴ ስዕሎችን እና ሌሎች መረጃዎችን በቀጥታ ለገቢዎች ሚኒስቴር ማስተላለፍ የሚያስችል፤

(ሐ) የገቢዎች ሚኒስቴር በስርአቱ ውስጥ በመግባት በዚያው ሰአት በስርአቱ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች እንዲያይ የሚያስችል፤

(መ) በማምረቻው ግቢ ውስጥ ያሉትን በሮች ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚያሳይ፤

(ሠ) የተሽከርካሪዎችን የሰሌዳ ቁጥር ጨምሮ የሚወጡ እና የሚገቡ የጭነት ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በግልጽ የሚያሳይ፤

(ረ) በፋብሪካው የሚመረቱ እቃዎች በመያዣ ውስጥ የሚታሸጉበትን መስመር፤ የሚታሸጉትን እቃዎች አይነት እና የማሸጊያውን መሳሪያ ፍጥነት ማየት የሚያስችል፤

(ሸ) የገቢዎች ሚኒስቴር በማናቸውም ጊዜ በስርአቱ ውስጥ በመግባት የጥሬ እቃን ጨምሮ የማናቸውንም እቃ እንቅስቃሴ በዚያው ሰአት እንዲያይ የሚያስችል፤

(ቀ) በመረጃ ስርአቱ ውስጥ ያሉት ምስሎች የተቀረጹበትን ቀን እና ሰአት በማይጠፋ እና በማይሻሻልበት ሁኔታ መዝግቦ የሚይዝ፤

(በ) ቴምብሮች ከአቅራቢው ተገዝተው ጥቅም ላይ እስኪውሉ የሚቀመጡበትን መጋዘን የሚያሳይ፤

መሆን አለበት።

14. <u>የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሳሪያዎች</u>

1/ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሳሪያዎች ጥሬ እቃዎችን እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች በሚለኩበት ጊዜ በትክክል መለካት የሚያስችሉ መሆን ያለባቸው ሲሆን፡-

(ሀ) ደረቅ ጥሬ ዕቃዎች ገቢ በሚደረጉበት ጊዜ ክብደታቸውን በትክክል የሚለካ ሚዛን ሊኖር የሚገባ ሲሆን በመዝገብ ውስጥ የሚመመዘገበው የፊዚካል ደረሰኝ ብቻ ይሆናል።

(ለ) በማከማቻ በርሜል ውስጥ ያለውን ፈሳሽ እንደ ማጣፈጫ ቅልቅል፣ ኤቲል አልኮል ወይም የቢራ ኮንሰንትሬት በሚመለከት ፈሳሹ በመቀበያው በርሜል ውስጥ ገቢ ከተደረገ በኋላ በርሜሉ ውስጥ በሚገባ መለኪያ ወይም በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ አማካኝነት መጠኑ ይለካል።

(ሐ) ዝግ በሆኑ በኢንዱስትሪ ደረጃ ባሉ በትላልቅ በርሜሎች ውስጥ ገቢ የሚደረጉ ፈሳሾችን ወይም ተመሳሳይ መቀበያዎችን በእቃ ማስረከቢያ ሰነድ ላይ የሰፈረውን ለማረጋገጥ መቀበያው መመዘን አለበት።

(መ) ደረቅ ጥሬ እቃ ከጥሬ እቃ ማከማቻ ውጪ ተደርጎ ወደ ማምረቻ ክፍል በሚሄድበት ጊዜ መመዘን አለበት።

(ሠ) ፈሳሽ ጥሬ እቃዎችን ለእያንዳንዱ የምርት ምድብ ወጪ የሚደረገው በፈሳሽ ሜትር መለካት አለበት።

(ረ) ምርቱ ከተመረተ በኋላ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የመጨረሻው ምርት ወደ መጀመሪያው ማከማቻ ሲጓጓዝ በፈሳሽ መለኪያ መለካት አለበት።

(ሰ) ለፍጆታ የሚውለው የመጨረሻው ምርት ከመታሸጉ በፊት ወደ መጨረሻው ማከማቻ ሲጓጓዝ እንቅስቃሴው በፈሳሽ ሜትር መለካት አለበት።

(ሸ) ፈሳሹ ወደ ማሸጊያው ክፍል በሚተላለፍበት ጊዜ እያንዳንዱ የማሸግ ተግባር በፈሳሽ መለኪያ መለካት አለበት።

(ቀ) በያንዳንዱ ማሸጊያ ውስጥ የገባው እና በፈሳሽ መለኪያ የተለካው ፈሳሽ መጠን ለገቢዎች ሚኒስቴር ሪፖርት ከተደረገው ታሽጎ ከወጣው እቃ ብዛት እና ብክነት ጋር መመሳከር አለበት።

(በ) የታሸጉ ምርቶች ወደ ተፈቀደለት አምራች መጋዘን በሚገቡበት ጊዜ ፈጣን ምላሽ ኮድ በማንበብ ክትትል የሚደረግባቸው ሊሆን ይገባል።

(ተ) እቃዎች ከመጋዘን ወጪ በሚደረጉበት ጊዜ ፈጣን ምላሽ ኮድ በማንበብ ክትትል የሚደረግባቸው ሊሆን ይገባል።

2/ አምራቹ የፈጣን ምላሽ ኮድ ቴክኖሎጂ የሌለው በሚሆንበት ጊዜ ይህንኑ ለገቢዎች ሚኒስቴር በማስታወቅ ግልጽ የሆነ የኦዲት ክትትል ማድረግ እንዲቻል እንደጉዳዩ ሁኔታ እየታየ ማኑዋል ቴክኖሎጂ እንዲጠቀም ስምምነት ሊደረስ ይችላል።

3/ ሲጋራን በሚመለከት ጥሬ እቃው ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሲጋራው እንደተመረተ ወዲያውኑ አውቶማቲክ የመቁጠሪያ መሳሪያው የታሸጉትን ሲጋራዎች ብዛት እና ሲጋራዎቹ የታሸጉበትን የሲጋራ ፓኬቶች ብዛት በትክክል መቁጠር አለበት።

4/ ትምባሆ በምርት ሂደት መልሶ ጥቅም ላይ የዋለ በሚሆንበት ጊዜ መልሶ ጥቅም ላይ የዋለው ትምባሆ ብዛት መመዝገብ አለበት።

5/ የፈሳሽ ሜትሮች እና የክብደት መለኪያዎች በአለምአቀፍ የደረጃዎች ድርጅት ማረጋገጫ (ISO) ወይም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የጥራት ማረጋገጫ ከተሰጠው አምራች መግዛት ያለባቸው ሲሆን በየሶስት ወሩ ስልጣን በተሰጠው ድርጅት በትክክል የሚሰሩ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

15. <u>የሂሳብ መዝገብ አያያዝ</u>

1/ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ለታክስ ከፋዩ የተሰጠው ደረጃ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የኤክሳይዝ ታክስ በሚመለከት ሁሉም ታክስ ከፋዮች የምርታቸው መጠን ሳይታይ በህግ የታዘዘውን ተመሳሳይ ሰነድ መያዝ እና ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

2/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች የሂሳብ አያያዙን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶች እና መረጃዎች መያዝ አለበት፦

ሀ) የጥሬ እቃ ግዢ ትእዛዝ ከተሰጠበት ሰነድ ጋር የተጣጣመ የጥሬ እቃ መቀበያ ሰነድ፣ የማስረከቢያ ሰነድ፣ በትክክል የተቀበለውን የተለካ ወይም የተመዘነ የጥሬ እቃው ዋጋ መጠየቂያ፣ ለጥሬ እቃው ክፍያ የተፈጸመበት ሰነድ፤

ለ) ወደ ጥሬ እቃ ማከማቻ መጋዘን ገቢ የተደረገውን ጥሬ እቃ መጠን፣ የጥሬ እቃውን የተለየ መለያ፣ የጥሬ እቃውን አይነት እና ብዛት፣ በመጋዘን ውስጥ ጥሬ እቃው የሚገኝበትን ቦታ፣ የአቅራቢውን ስም፣ የማስረከቢያ ሰነድ ቁጥር፣ የትእዛዙን ቁጥር፣ ቀን እና ፊርማ የያዘ የውስጥ ዝውውር ሰነድ፤

ሐ) ከውስጥ ዝውውር ሰነድ ጋር የተጣጣመ፣ የጥሬ እቃውን የተለየ መለያ፣ የጥሬ እቃውን አይነት እና ብዛት፣ ከመጋዘን ውስጥ ጥሬ እቃው ወጪ የተደረገበትን ቦታ፣ የምርቱን ምድብ ቁጥር፣ የሚመረተውን ምርት መለያ ስም፣ ጥሬ እቃው ወጪ የተደረገበትን ቀን፣ ሰአት እና ፊርማ የያዘ ሰነድ፤

መ) ከጥሬ እቃ መጋዘን ወጪ የተደረገው ጥሬ እቃ መጠን፣ ለታቀደለት የምርት ምድብ የዋለ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ የሚመዘገብበት ጥሬ እቃው ወደ ምርት ሂደት የገባበትን ሂደት የሚያሳይ ሰነድ፤

ሠ) ሙቀት መለካትን፣ ተጨማሪ ወይም ተለዋጭ ነገሮችን ማከልን ጨምሮ በምርት ሂደት ውስጥ ያሉት የምርቱ ደረጃዎች የሚመዘገብበት ሰነድ፤

ረ) በምርቱ ምድብ ቁጥር ጥቅም ላይ ከዋለው ጥሬ እቃ ጋር የተዛመደ፣ ከምርት በኋላ ባለው የመጀመሪያ ማከማቻ በጥቅል የተያዙትን ፈሳሾች ብዛት (አልኮል ያለው ወይም የሌለው ቢሆንም) የሚያሳይ መረጃ ፤

ሰ) የማሸጊያ ትእዛዙን ቁጥር፣ የታሸገው እቃ ብዛት፣ ጥቅም ላይ ከዋለው ጥቅል ፈሳሽ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚያሳይ፣ የማሸጊያ ትእዛዙን ቁጥር የያዘ ወደ ማሸጊያ የተላከውን ጥቅል ፈሳሽ የሚያሳይ፣ ትክክለኛ የታሸገው የመጨረሻ ምርት ወደ ማሸጊያ የተላከውን ጥቅል ፈሳሽ የሚያሳይ ትክክለኛ መረጃ፤

ሸ) ማናቸውም ሲጋራ በሚታሸግበት ጊዜ በአውቶማቲክ መሳሪያ የተቆጠረውን ሲጋራ ብዛት፣ በምርት ሂደት ሲጋራው ወይም ፓኬቱ የተሰበረ እና መልሶ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ የዚህ ብዛት የተመዘገበበት ሰነድ፤

ቀ) ወደ መጋዘን የገባን ማናቸውም ምርት ስም፣ የመያዣውን መጠን፣ ምርቱ ለኤክሳይዝ ታክስ አላማ የተሰጠውን ምደባ የያዘ የምርት ቁጥር ፤

በ) ወደ መጋዘን የገቡ የታሸጉ ምርቶችን ከምርት ምድብ ቁጥር እና ጥቅም ላይ ከዋለው ጥሬ እቃ ጋር በማዛመድ የተከናወነ ምዝገባ ፤

ተ) ከፋብሪካ የሚወጡ ምርቶችን በሚመለከት የግዢውን ትእዛዝ፣ የደንበኛውን ስም፣ የማስረከቢያ ሰነድ፣ ደረሰኙን፣ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ እና እቃው የሚላክበትን ቦታ ጭምር ያያዘ ሰነድ፤

3/ የተመረተውን የመጨረሻ ምርት ጥቅም ላይ ከዋለው ጥሬ እቃ ጋር የሚያገናኝ የተለየ ቁጥር መኖር ያለበት ሲሆን ይህም የግዢውን ትእዛዝ፣ የትእዛዝ ቁጥር ወይም የተለየ ኮድ የያዘ ሊሆን ይችላል።

4/ እያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ አምራች በእያንዳንዱ ወር በ30ኛው ቀን የሚከተሉትን የሚያሳይ መረጃ ለታክሱ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት።

ሀ) የእያንዳንዱን ምርት ኮድ የማምረቻ ወጪ በዝርዝር የሚያሳይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን የእያንዳንዱን የምርት ኮድ ዋጋ የያዘ የዋጋ ዝርዝር፤

ለ) የዋጋ ዝርዝሩ ለእያንዳንዱ የምርት ኮድ ከምርቶች ስሌት ዋጋ ጋር መያያዝ ያለበት ሲሆን ይህም እያንዳንዱ የወጪ አካል ለብቻው መዘርዘር አለበት።

ሐ) ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ የያዘ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ፤

5/ በየወሩ የሚፈጸመው የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያም በእያንዳንዱ ወር በ30ኛው ቀን ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ መደረግ አለበት።

6/ በየወሩ ሊቀርብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ቅጽ በጊዜው ያለማቅረብ እና ታክሱን ያለመክፈል በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣትን ያስከትላል።

16. <u>ለሙከራ የሚመረቱ ምርቶች</u>

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሙከራ ለማምረት የሚፈልግ የተፈቀደለት አምራች የሚከተሉትን መረጃዎች ለገቢዎች ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት፦

(ሀ) የሚመረተውን ምርት አይነት፤

(ለ) የማምረቻውን ወጪ እና ለኤክሳይዝ ታክስ አላማ የእቃውን ዋጋ፤

(ሐ) ሙከራ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያት፤

(መ) የሙከራ ምርቱን ብዛት፤

(ሠ) የሙከራውን ባህሪ፤

(ረ) የሙከራው ምርት ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት መሆኑን፤

(ሰ) ከኤክሳይዝ ታክስ ነጻ የሚሆነውን ለላቦራቶሪ ትንተና ወጪ የሚደረገውን የሙከራ ምርት ብዛት፤

2) ለሙከራ የሚመረት ምርት በማናቸውም ሁኔታ ከአንድ ወር በላይ የሚቆይ ሊሆን አይችልም።

3) የሙከራ ምርት በሚመረትበት ጊዜ የአመራረቱን ሂደት እና ምርቱ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ መያዝ አለበት።

## 17. <u>አስቀድሞ በተደረገ የሽያጭ ውል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ወጪ ማድረግ</u>

1/ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ ተደርገው ለታወቀ ገዢ የሚላኩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የእቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥላቸው ይገባል።

2/ የእቃ ማስረከቢያ ሰነድ በሶስት ቅጂ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን የመጀመሪያው ቅጂ እቃው ወጪ በተደረገበት ፋብሪካ፣ ሁለተኛው እና ሶስተኛው ቅጂ እቃውን ከሚያጓጉዘው ተሽከርካሪ ጋር መላኩ እንደተጠበቀ ሆኖ እቃው በመድረሻ ቦታው ሲደርስ ሁለተኛው ቅጂ ለደንበኛው ይሰጣል፣ ሶስተኛው ቅጂ በደንበኛው ተፈርሞበት እቃው ደንበኛው ዘንድ የደረሰ ለመሆኑ ማረጋገጫ እንዲሆን እቃው ወጪ ወደ ሆነበት መጋዘን ይመለሳል።

3/ በአንቀፅ 17(2) የተገለፀው የእቃ ማሰረቢያ ሰነድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 የተዘረዘሩትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል።

4/ የእቃ ማስረከቢያ ሶስተኛው ቅጂ እቃው ወጪ ወደ ተደረገበት የማምረቻ ቦታ ወጪ በተደረገ በአንድ ቀን ውስጥ መመለስ ያለበት ሲሆን የሰነዱን ቅጂ በኢ.ሜል መላክ ይቻላል።

18. <u>ሽያጭ ሳይፈጸም የተመረተውን ምርት ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ</u>

1/ ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ ሽያጭ የሚከናወነው ከፋብሪካው ውጪ ከሆነ፤ እቃው ከፋብሪካ ሊወጣ የሚችለው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ የማስረከቢያ ሰነድ ከተቆረጠ በኋላ መሆን አለበት።

2/ የእቃው ሽያጭ የሚከናወነው ምርቱን ከፋብሪካ ውጪ በተሽከርካሪ በማዘዋወር ወይም ከፋብሪካ ውጪ ባለ የሽያጭ መጋዘን ከሆነ ሾፌሩ ወይም የሽያጭ ሰራተኛው እንደ አግባብነቱ የሚከተሉትን መረጃዎች መመዝገብ አለበት፤

(ሀ) እቃው የተሸጠለትን ደንበኛ ስም፤

(ለ) እያንዳንዱ እቃ የተሸጠለትን ደንበኛ አድራሻ፤

(ሐ) የእያንዳንዱን ሽያጭ መረጃ፤

(መ) በመኪና ተዘዋውሮ ለሚሸጥ ሽያጭ ያልተከናወነ ከሆነ ሽያጭ ያልተከናወነ መሆኑን፤

(ሠ) ሽያጭ የተከናወነ ከሆነ የሽያጩ ደረሰኝ የተሸጠውን እቃ ዝርዝር መረጃ እና የተሸጠበትን ዋጋ እና የማስረከቢያ ሰነዱን ቁጥር መያዝ አለበት።

(ረ) ሽያጩ በተከናወነበት ጊዜ የሽያጩ ዋጋ ወዲያውኑ መከፈል ያለበት ሲሆን ደረሰኝ ሊቆረጥ ይገባል።

3/ ምርቱን በተሽከርካሪ በማዘዋወር የሚሸጥ ሾፌር ወደ መስሪያ ቤቱ ሲመለስ በታክስ ደረሰኙ ላይ የተመለከተው የተሸጠ እቃ ብዛት እና ተመላሽ የተደረገው እቃ ብዛት መመሳከር አለበት።

4/ ሳይሸጥ የተመለሰው እቃ የመቀበያ ሰነድ ተቆርጦ ወደ መጋዘን ተመላሽ ከተደረገ በኋላ በተለየ ቦታ መቀመጥ ያለበት ሲሆን በሌላ ጊዜ ለሽያጭ እንዲውል ይደረጋል።

19. <u>የማስረከቢያ ሰነድ ይዘት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 እና 18 በተደነገገው መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ ከፋብሪካ ሲወጣ የሚቆረጠው የማስረከቢያ ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ) የተለየ መለያ ቁጥር፤

ለ) የአምራቹን ስም፤

ሐ) እቃው ወጪ የተደረገበት አድራሻ፤

መ) እቃው የተላከበት ቀን እና ሰአት፤

ሠ) የደረሰኝ ቁጥር ( አስቀድሞ የተሸጠ ከሆነ)

ረ) የደንበኛው ስም( አስቀድሞ የተሸጠ ከሆነ)፤

ሰ) ለደንበኛው እቃው የሚላክበት አድራሻ ( አስቀድሞ የተሸጠ ከሆነ)

ሸ) የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር

ቀ) የሾፌሩ ስም

በ) የተለየ መለያ ቁጥር

ተ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት አይነት

ቸ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ ኮድ፤

ኃ) የእያንዳንዱ ምርት ምድብ/አይነት ብዛት፤

ነ) በእያንዳንዱ መያዣ ውስጥ ያለው ብዛት፤

ኘ) መያዣው ጠርሙስ፤ ቆርቆሮ ወይም በፖኬት ወዘተ፤

አ) እቃው ወጪ በተደረገበት ቦታ ያለው ሰራተኛ ፊርማ የሚያርፍበት ሳጥን፤

ከ) የሾፌሩ ፊርማ የሚያርፍበት ሳጥን፤

20. <u>የጅምላ ሻጮች እና የቸርቻሪዎች ግዴታ</u>

1/ ጅምላ ሻጮች እና ቸርቻሪዎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ከመረከባቸው በፊት፡

(ሀ) በምርቱ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ፊዚካል ወይም ዲጂታል ቴምብር የተለጠፈበት መሆኑን የማረጋገጥ፤

(ለ) የፈጣን ምላሽ ኮዱን ለማንበብ የሚያስችል መተግበሪያ በማውረድ ፈጣን ኮዱን በማንበብ የምርቱን ምንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመላከተውን ግዴታ ያልተወጣ ሰው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 በተደነገገው መሰረት አስተዳደራዊ እና የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል።

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የፈጣን ምላሽ ኮድ" ማለት በማሸጊያው ውስጥ ያለውን ምርት አምራች፣ የምርቱን ይዘት፣ የተመረተበትን ቦታ፣ ቀን እና ሰአት፣ የመጠቀሚያውን ጊዜ ጨምሮ ሌሎች ተመሳሳይ መስፈርቶችን ሊጨምር የሚችል በኤሌክትሮኒክስ የሚይዝ ምልክት ነው።

21. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገቢዎች ሚኒስቴር ይፋዊ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ፤ ግንቦት 2017 ዓ.ም

አይናለም ንጉሴ አሊ
የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

## አባሪ

| ተ.ቁ | የኤክሳይዝ ታክስ ሊለጠፍባቸው የሚገባ እቃዎች | መያዣዎች | መጠን | ስርዓት | የኤክሳይዝ ቴምብር ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ቢራ (በአነስተኛ መያዣ) (የአገር ውስጥ ቢራን ጨምሮ) | የጠርሙስ ወይም የቆርቆሮ መያዣ | ልዩ ልዩ | ፈጣን የማምረቻ መስመር | ዲጂታል |
| 2. | ቢራ (በከፍተኛ መያዣ) (የአገር ውስጥ ቢራን ጨምሮ) | በርሜል | 20 ሊትር፤ 50 ሊትር | ማንዋል | ፊዚካል |
| 3. | አልኮል የሌለው ቢራ | ጠርሙስ | ልዩ ልዩ | ፈጣን መስመር | ዲጂታል |
| 4. | ወይን እና አልኮል የተጨመረበት ወይን ጠጅ፣የአልኮል መጠጥ | ጠርሙስ ፡ በካርቶን ውስጥ ያለመያዥ | ልዩ ልዩ | ፈጣን ያልሆነ/ ማንዋል | ዲጂታል/ ፊዚካል |
| 5. | ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ መልክ የተመረቱ መጠጦች | ቆርቆሮ/ ጠርሙስ | በመደበኛነት 250 እና 300 ሚሊ ሊትር | ቆርቆሮው ፈጣን ነው | ዲጂታል/ ፊዚካል |
| 6. | የታሸገ ውሃ | ጠርሙስ/ጀር | ልዩ ልዩ | ይለያያል | ዲጂታል/ ፊዚካል |
| 7 | ሽቶዎች | የጠርሙስ ወይም የቆርቆሮ መያዣ | ልዩ ልዩ | ይለያያል | ዲጂታል/ ፊዚካል |
| 8. | አልኮል የሌለባቸው ስኳር በማጣፈጫነት የተጨመረባቸው መጠጦች | ጠርሙስ | ባመዛኙ ከ250 ሚሊ ሊትር እስከ 2 ሊትር | ፈጣን በትላልቅ ኩባንያዎች | ዲጂታል |
| 9 | ሲጋራ | 20 ሲጋራ የሚይዝ ፓኬት | ባለ 20 ሲጋር ፓኬት | አውቶማቲክ | ዲጂታል/ ፊዚካል |
| 10 | ሌሎች የትምባሆ ምርቶች | ልዩ ልዩ | ልዩ ልዩ | ፈጣን ያልሆነ | ፊዚካል |